**ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

**ሰበር ሰሚ ችሎት**

የመ/ቁ 17191

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ

አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ

አቶ አብዱልቃድር መሐመድ

ወ/ሮ ስንዱ አለሙ

ወ/ት መስፍን አቁበ ዮናስ

አመልካች፡- አስቴር አርአያ

መልስ ሰጭ፡-  አቶ ግርማ ወዳጆ

*ውል - የውል ጉዳይ  አወሳሰን - ስለ ውሎች ውጤት ውለን በመተርጐም ሰበብ ደኞች አንድ ውል ሊፈጥሩ ስላለመቻላቸው - ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ለዩ ለዩ ደንቦች  የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥሮች 1711፣1731፣1676/2/፣2635፣2640፣2646*

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካከ ባቀረበችው ክስ በጠየቀችው መሠረት ተጠሪ አመልካች ከከፈለው ብር 35,000/ ሰላሣ አምስት ሺህ/ በተጨማሪ በፍርዱ ከተገኘው ጥቅም 20% ብር 124,188.59 /አንድ መቶ ሃያ አራት ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም/ ለአመልካች እንዲከፍል ሲወስን ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ አመልካች ለሰጠችው አገለግሎት ካገኘችው መደበኛ ክፍያ በተጨማሪ በፍርድ ከሚገኘው ጥቅም 20% ታስቦ እንዲከፈላት በውል የተደረገው ቃል በፍትህ ሆነ በርትዕ የሚደገፍ አይደለም በሚል የከፍተኛውን ፍ/ቤት ውሣኔ በመሻሩ የቀረበ አቤቱታ



ውሳኔ፤- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ ተሻሽሏል፡፡

1. ህግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደፈለጋቸው የመወሰን መብት ያላቸው ሲሆን በዚህ መሰረት የሚደረጉ የውል ስምምነቶች በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንደ ህግ ሆነው ይቆጠራሉ፡፡
2. ሆኖም ልዩ የዕውቀት ያላቸውን የስራ ውሎች የሚያደርጉ ተዋዋዮች ስምምነት ላይ የደረሰባቸው የስራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ መሆናቸው ግልፅ በሆነ ጊዜና ለሙያ ስራ ተግባሩም ክብር ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ መጠኑን ዳኞች በመሰላቸው ሊቀንሱት ይችላሉ፡፡

## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት
## ሰበር ችሎት

የመ/ቁ17191
ሐምሌ 29 ቀን 1997

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ፍሰሐ ወርቅነህ
አቶ አብዱልቃድር መሐመድ
ወ/ሮ ስንዱ አለሙ
አቶ መስፍን ዕቁበ ዮናስ

አመልካች፡- ወ/ሮ አስተር አርአያ

ተጠሪ፡- አቶ ግርማ ወዳጆ

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በሰበር ችሎቱ ለቀረበው ጉዳይ መነሻ የሆነው ክስ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን የአሁኗ አመልካች ለተጠሪ በሰጡት የጥብቅና አገልግሎት ሥራ የካቲት 3 ቀን 1987 በተደረገው የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ውል መሠረት በማድረግ ተጠሪ ለአመልካች ከከፈለው ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ ብር) በተጨማሪ "ከፍርዱ ከሚገኝ ጥቅም 20% ሊከፍል የተስማሙበትን ብር 520,000 (አምስት መቶ ሃያ ሺህ ብር) አመልካች በክሱ ምክንያት ካወጣው ወጭና የጠበቃ አበል ጋር ይከፈል በማለት ክስ መስርቷል፡፡

ፍርድ ቤቱም ግራቀኙን አከራክሮ የአሁኑ ተጠሪ "ጥቅም" አላገኘሁም በሚል በሙያ አገልግሎት ውሉ የተስማማበትን ክፍያ አልከፍልም ማለቱ አግባብ አለመሆኑን ገልጾ፣ የቤቱን ሽያጭ ዋጋ ግምት መሠረት በማድረግ 124,188.59 (አንድ መቶ ሃያ ራት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም) የዳኝነቱንና የጠበቃ አበሉን ጨምሮ ይከፈል በማለት ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ፣ አንድ የጥብቅና ሙያ አገልግሎት የሚሰጥ ሙያተኛ ለአገልግሎቱ እንዲከፈለው ከተወሰነለት መደበኛ የክፍያ በተጨማሪ "ከፍርድ ከሚገኘው ጥቅም" ታስቦ እንዳከፈለው የሚደረግ የውል ቃል በርትዕም ሆነ በፍትህ የሚደገፍ አይደለም በማለት የሥር ፍቤትን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ሽሮታል፡፡



የአሁን አመልካች በሰበር እንዲታይላት ያቀረበችው ማመልከቻ የሕግ ትርጉም የሚያስነሱ ነጥቦች ያሉት መሆኑን በማመን ጉዳዩ ለሰበር እንዲቀር ተደርጓል፡፡ በዚህ መሠረት ተጠሪ መልሷን አመልካች ደግሞ የመልስ መልሱን እንዲያቀርቡ ተደርጐ ክርክሩ አብቅቷል፡፡

ይህ የሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ በዋናነት የሕግ ትርጉም የሚያስፈልገው ጭብጥ የእውቀት ጠባይ ያላቸው የሥራ ውሎችን አስመልክቶ በተዋዋይ ወገኖች መካከል ስምምነት በተደረሰባቸው የክፍያ መጠኖች ላይ አለመግባባቶች ሲነሱ የዳኞች ሚና ምን ይሆናል? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

እንደሚታወቀው ማንኛውም ውል በተዋዋይ ወገኖች ፈቃድ ላይ ተመስርቶ የማደረግ ስምምነት ነው፡፡ ሕግ ከወሰናቸውና ከከለከላቸው ነገሮች ውጭ ተዋዋይ ወገኖች የሚዋዋሉበትን ጉዳይ እንደመሰላቸው የመወሰን መብት ያላቸው መሆኑን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1711 ያስገነዝባበናል፡፡ ውሉን ለመዋዋል ሕጉ በሰጠው ነፃነት መሠረት የሚደረገው የውል ስምምነቶች በግራ ቀኝ ተዋዋይ ወገኖች መካከል መብትና ግዴታዎች የሚጥሉ በመሆናቸው ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ እንደ ሕግ ሆነው የሚያገለግሉ መሆናቸውን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 መገንዘብ ይቻላል፡፡

በያዝነው ጉዳይ የአሁኗ አመልካችና ተጠሪ የካቲት 3 ቀን 1987 ዓ.ም የጥብቅና ሙያ አገልግሎት ውል ያደረጉ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በዚህ ውል ስምምነት መሠረት ተጠሪ በሕገወጥ መንገድ ተይዞብኛል የሚለውን ቤት በማስመለስ ረገድ የአሁኗ አመልካች ለምታበረክተው ሙያዊ የጥብቅና አገልግሎት ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ ብር) ለመክፈልና ከፍርዱ ከሚገኘው ጥቅም 20% ለመክፈል የተስማሙ መሆኑን ከሥር መዝገቡ ተረድተናል፡፡ በዚህ የውል ስምምነት ቤት የተመለሰለት የአሁኑ ተጠሪ ብር 35,000 (ሠላሣ አምስት ሺህ) ለአመልካች የከፈለ ቢሆንም ከፍርድ ከሚገኘው ጥቅም ለመክፈል የተስማሙበትን 20% እንዲከፍል ክስ በቀረበበት ጊዜ «ጥቅም» አላገኘሁም በሚል ሲከራከር የቆየ ቢሆንም ጉዳዩን የመረመረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሉን መሠት በማድረግ የንብረቱን ግምት አስልቶ ተጠሪ ብር 124,188.59 (አንድ መቶ ሃያ ራት ሺህ አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከሃምሣ ዘጠኝ ሣንቲም) እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከፍ ሲል የገለጽነውን የውል ሕግ መሠረታዊ መርህ የሆነውን "በፍቃደኝነት ወደ መዋዋልን" መሠረት አድርጐ ውሣኔ የሰጠ ቢሆንም

የዚህ መርህ አፈጻጸም በፍትሐብሔር ሕጉ ውስጥ አግባብ ካላቸው ልዩ ድንጋጌቻች ጋር እንዴት መገናዘብ እንደሚገባው ሳይመረምር ከውሣኔ እንደደረሰ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ በግራቀኙ መካከል በሕጋዊ መንገድና በፈቃደኛነት የተቋቋመን ግልጽ ውል ትርጉምንና ርትዕን ምክንያት በማድረግ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ.1711፣1714(2) እና 1733 ከሚደነግጉት ውጭ እና በወቅቱ በሥራ ላይ ያልነበረን ደንብ ዋቢ በማደረግ «ከፍርድ የሚገኘውን ጥቅም» ለሙያዊ አገልግሎት በሚደረግ ስምምነት ውስጥ ሊጠየቅ አይገባም በማለት ተዋዋይ ወገኖች በስምምነት ያስቀመጡትን ግልጽ የውል ቃል ያለምንም የዉል ማፍረሻ ምክንያት ውድቅ እንዲሆን ማድረጉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከፍ ብለን ለማሳየት እንደሞከርነው የየትኛውም ሕጋዊ ውል መሠረቱ በፈቃድ መስጠት ላይ የተመሠረተ ስምምነት መሆኑ አያከራክርም፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ሕጉ በሰጣቸው ነፃነት ተጠቅመው ንብረትነትን የሚመለከቱ ግዴታዎችን ለማቋቋም ለመለወጥ ወይም ለማስቀረት ስምምነት ማድረግ እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡ ይህ በጠቅላላ ክፍሉ የተነገረው የውል መሠታዊ መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ እነዚህን ጠቅላላ ደንቦች የሚለውጡ ወይም የሚያሟሉ ስለ አንዳንድ ውሎች የተጻፉ ልዩ  የሆኑ ደንቦች ካሉ በፍትሐብሔር ሕግ 5ኛ መጽሐፍ እና በንግድ ሕጉ የሚመለከቱ ስለመሆኑ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 1776(2) ያስገነዝባል፡፡

በዚህም መሠረት አሁን ግራቀኙ እየተከራከሩበት ያለው ሙያዊ የዕውቀት ሥራ የሚመለከት ውል በፍትሐብሔር ሕጉ 5ኛ መጽሐፍ ውስጥ ከሚገኙት ሌሎች መካከል አንደኛ እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ ልዩ የእውቀት ጠባይ ያላቸው የሥራ ውሎች ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2632 እና በሚቀጥሉት ቁጥሮች ውስጥ በተመለከቱ ድንጋጌዎች የሚመሩ ናቸው፡፡ እነዚህ የውል አይነቶች ልዩ ዕውቀትን የሚመለከቱ በመሆናቸው የተለየ ስምምንት ከሌለ በቀር የእውቀት ሥራውን የተዋዋለው ሰው ግዴታዎቹን ራሱ መፈፀም እንደሚጠበቅበት ከሕጉ ቁጥር 2636(1) መገንዘብ ይቻላል፡፡

ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ፈቅዶ የመዋዋል መርህን ተጠቅመው እነዚህን አይነት መሰል ውሎች መዋዋል ቢችሉም በነዚህ ልዩ ውሎች መሠረት ስምምነት ላይ



የተደረሱባቸው የሥራ ዋጋዎች ከመጠን በላይ መሆናቸው ግልጽ በሆነ ጊዜ እና ለሙያ ሥራ ተግባሩም ክብር ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የሥራ ዋጋ መጠኑን ዳኞች በመሰላቸው ሊቀንሱት እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡ የዚህ ሕግ  አይነተኛ ዓላማ የተለየ እውቀት በሚሻው ጉዳይ ዙሪያ አማራጭ የሌለውን ወይም አማራጩ በእጅጉ ሊጠብበት የሚችለውን ተዋዋይ ወገን የሙያውን ተግባር ከሚያከናውነውና ልዩ እውቀት ካለው ሙያተኛ ተዋዋይ ወገን ጋር ውልን ፈቅዶ በመዋዋል ረገድ የሚኖረውን ቦታ (position) በተቻለ መጠን ለማቀራረብ እንደሆነ ይገመታል፡፡ በዚህ ረገድ በአብነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ጉዳዮች መካከል ከቀዳጅ ሀኪሞች፣ ከጥርስ ሐኪሞች ወይም ከአእምሮ  በሽታ ሐኪምች እና ሰዎችን ከማከም ኪነጥበብ ጋር ተያይዘው የሙያቸውን ተግባር የሚያከናውኑ ሰዎች ከበሽተኞቻቸው ወይም ከወኪሎቻቼው ጋር ባደረጉዋቸው ውሎች መነሻነት ስምምነት የተደረሰባቸው የሥራ ዋጋዎች ከመጠን  በላይ ሆነው በተገኙ ጊዜ እና ሕይወትን መታደግን ዋንኛ ሙያዊ መርህ አድርጎ ከተነሣው የዋጋውን መጠን ሊያሻሽሉት እንደሚችሉ የፍት.ሕግ ቁጥር 2640 እና 2646 ይደነግጋሉ፡፡

በያዝነው ጉዳይ ግራቀኙ የልዩ ዕውቀት ፀባይ ያለው አገለግሎት ሥራ ውል ያደረጉ መሆኑ ይታመናል፡፡ ንብረቱ የተወሰደበት የአሁኑ ተጠሪ ለሚሰጠው ሙያዊ አገልግሎት በውሉ የተመለከተውን ብር 35,000 እና በፍርድ ከሚገኘው ጥቅም 20% ለመስጠት ተስመቶ የነበረ መሆኑን ይህ ችሎት በሚገባ ተገንዝቧል፡፡ ይህ ስምምነት ውልን ፈቅዶ በመዋዋል መርህ ላይ ተመስርቶ የተደረገ ውል አይደለም ለማለት እንኳን የሚያስችል ነገር ባይኖርም ከፍ ብለን ከላይ ሕጉ ሊጠብበቃቸው ከተነሳው ዓላማ አኳያ ጉዳዩን በጥልቀት ስንመረምረው የአሁኗ አመልካች በሥር ፍ/ቤት ለሰጠችው ሙያዊ አገልግሎት 35,000 (ሰላሣ አምስት ሺህ) የተከፈላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ ክፍያ ከንብረቱ ግምት አኳያ በመቶኛ ሲሰላ 17% ይሆናል፡፡ አሁን አመልካች በተጨማሪ እንዲከፈላት እየጠየቀች ያለችው 20% ከቀድሞ ክፍያ ጋር ሲደመር የጠቅላላ ቤቱን ግምት 37% መሆኑ ታውቋል፡፡ የተጠየቀው የገንዘብ መጠን ደግሞ ከንብረቱ ዋጋ ጋር ሲነጻጸር በተለምዶ ለአገልግሎቱ ከሚጠየቀው ክፍያ ጋር ሲታይ እጅግ በጣም የተጋነነና ለሙያውም ሥራ ክብር ቢሆን ተቃራኒ የሆነ መሆኑን አምነንበታል፡፡

በመሆኑም ስምምነት የተደረሰበት የሥራ ዋጋ መጠን የበዛ እና ለሙያ ሥራ ክብርም ተቃራኒ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ዳኞች መጠኑን እንዲቀንሱ ሕጉ የሰጣቸውን ሥልጣን በመጠቀም የአሁኑ ተጠሪ ለአመልካች የንብረቱን ግምት ማለትም የብር 620,942.98

(ስድስት መቶ ሃያ ሺህ ዘጠሀን መቶ አርባ ሁለት ብር ከዘጠና ስምንት ሣንቲም) 10% (አሥር በመቶ) የሆነውን ገንዘብ እንዲከፍል ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች ቀደም ሲል በውሉ መሠረት የወሰደው ብር 35,000 ከክፍያው ገንዘብ ላይ ተቀናሽ ሊሆን የሚገባ መሆኑን አምነንበታል፡፡

**ው ሣ ኔ**

- ተጠሪ ብር 27,094.30 (ሃያ ሰባት ሺህ ዘጠና አራት ብር ከሠላሣ ሣንቲም) ይህ ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ሕጋዊ ወለድ ጋር ለአመልካች ይከፈል፣
- የዚህ ፍ/ቤት ወጪና ኪሣራ ግራቀኙ ይቻቻሉ፣
- የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሐምሌ 8 ቀን 1996 ዓ.ም በፍ/ብ/ይ/ቁ 14821 የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡

  መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች

## ቅፅ 2

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ህዳር 1998 ዓ.ም.
አዲስ አበባ